# 181st Semiannual General Conference
## Sunday Morning Session, October 2, 2011

የስም አስፈላጊነት

በሽማግሌ ኤም ራስል ባለርድ

የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል

በዚህች ወብታማ ሰንበት አብረን ስናመልክ ከእናንተ ጋር መሆኔ መልካም ነው። ካለፈ ሚያዝያ አጠቃላይ ጉባኤ ጀምሮ፣ አዕምሮዬ በስም አሥፈላጊነት ርዕስ ላይ ሲያተኩር ነበር። ባለፊት ጥቂት ወሮች፣ የልጅ ልጂቼ ልጆች ወልደዋል። ምንም እንኳን በፍጥነት የሚወለዱ ቢመስልም፣ እያንዳንዱም ወደ ቤተሰብ በደስታ እንቀበላቸዋለን። በህይወታቸው በሙሉ የሚታወቁበት፣ ለእነርሱም ልዩ የሆነ ስም በወላጆቻቸው ተመርጦላቸው ነበር። ይህም በሁሉም ቤተሰብ ይደረጋል፣ እናም በአለም ሀይማኖት ውስጥ በሙሉም ይህም እውነት ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእነዚይ በመጨረሻው ቀናት ቤተክርስቲያኗን ግልፅ ስም መስጠቱ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ አውቅ ነበር። በት/ቃ 115 ውስጥ ቤተክርስቲያኑን ስም ሰጣት፥ "በመጨረሻ ቀናትም በዚህ፣ እንዲሁም በየኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ስምነው ቤተክርስቲያኔ የምትጠራው።"

ንጉስ ቢንያምም በመፅሐፈ ሞርሞን ዘመን ህዝቡን እንዲህ አስተማረ፥

"…ስለዚህ የክርስቶስን ስም እንድትወስዱ እፈልጋለሁ፣ ሁላችሁም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን የገባችሁ እስከህይወታችሁ መጨረሻ ታዛዥ እንድትሆኑ እመኛለሁ።

"እናም ይህን ደግሞ እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ፣ በመተላለፍ ካልሆነ በቀር ለእናንተ መስጠት አለብኝ ያልኩት የማይደመሰሰው ስም ይህ ነው፤ ስለዚህ፣ ስሙም ከልባችሁ እንዳይጠፋ ዘንድ እንዳትተላለፉ አስተውሉ።" (ሞስያ 5፡ 8፣ 11)

በጥምቀት ውሀ ውስጥም የክርስቶስን ስም እንወስዳለን። በየሳምንቱም ቅዱስ ቁርባንን ስንወስድ፣ የዚህን ጥምቀት ውጤታ እናሳድሳለን፣ በዚህም ስመር በራሳችን ላይ ለመውሰድ እናም እርሱን ለማስታወስ ቃል ለመግባት ፈቃደኞች እንደሆንን እናሳያለን። (ት እና ቃ 20፡ 77፣ 79 ተመልከቱ)

የእግዚአብሔርን ተወዳጅ እና አንድያ ልጅ ስም በመውሰዳችን እንዴት እንደተባረክን ይገባናል? ይህ እንዴት ታላቅ ትርጉም ያዘለ እንደሆነ ይገባችኋል? ከሰማይ በታች ከሚገኙት ስሞች ሁሉ ሰውሊድንበት የሚችለው በአዳኝ ስም ብቻ ነው። (2ነፊ 31፥ 21 ተመልከቱ)

እንደምታስታውሱት፣ ባለፈው ሚያዝያ አጠቃላይ ጉባኤ ፕሬዘደንት ፓከር ስለቤተክርስቲያኗ ስም አስፈላጉነት ተወያይተው ነበር። እንዲህም ገለጹ፣ "ለራዕይ ታዛዥ በመሆን፣ እራሳችንን የሞርሞን ቤተክርስቲያን ሳይሆን የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ብለን እንጠራለን።"

የቤተክርስቲያኗ ሙሉ ስም አስፈላጊ ስለሆነ፣ የቤተክርስቲያኑ አባላት የቤተክርስቲያኗ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደምትታወቅ እንዲጠብቁና አለምን እንዲያስተምሩ በቅዱሳት መሳህፍት የተገለጹትን፣ በቀዳሚአመራ ከ 1982 እስከ 2001

ድረስ የላኩትን መመሪያዎች፣ እና የነቢያትን ቃላት እንደገና እናገራለሁ። ጌታ በመጨረሻው ቀናት የሚጠራን ስም ይህ ነው። ይህም ቤተክርስቲያኑ እራሷን ከሌሎች ልዩ የምታደርግበት ስም ነው።

አዳኝ በዳግም ለተመለሰችው ቤተክርስቲያኑ ለምር ረጅም ስም እንደሰጠ አስቤበት ነበር። ረጅም ይመስላል፣ ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ምን እንደሆነች እንደሚገለጽበት ከተመለከትነው፣ ይህም ቀጥተኛ፣ አጭሬ፣ እና ግልፅ ይሆናል። እንዴት መግለጫ ቀጥተኛና ግልፅ ሆኖ፣ በትንሽ ቃላት ለመገልፅ ይቻላል?

እያንዳንዱ ቃላት ግልፅ የሚያደርጉና ሊተዉ የሚቻሉ አይደሉም። ስሟ በዳግም የተመለሰው ቤተክርስቲያን ከአለም ሀይማኖቶች ጋር የት እንደምትቆም የሚያሳይ ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚሉት ቃላት የእርሱ ቤተክርስቲያን እንደሆነው የሚያውጅ ነው። በመፅሐፈ ሞርሞን ውስጥ ኢየሱስ እንዳስተማረው፣ "እናም በስሜ ካልተጠራ[ሀ] የእኔ[ለ] ቤተክርስቲያን እንዴት ሊሆን ይችላል? ቤተክርስቲያኗ በሙሴ ስም ከተጠራች የሙሴ ቤተክርስቲያን ትሆናለች፤ ወይም በሰው ስም ከተጠራች የሰው ቤተክርስቲያን ትሆናለች፤ ነገር ግን በወንጌሌ ላይ የተገነቡ ከሆኑ፣ በስሜ ከተጠራች የእኔ ቤተክርስቲያን ትሆናለች።" (3 ኔፊ 27፥ 8)

የኋለኛው ቀን የሚቀልጸው ይህች ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ በሚያስተምርበት ጊዜ የአሰረተው ቤተክርስቲያን በኋለኛው ቀናት በዳግም እንደተመለሰች ነው። እውነተኛው እና ፍጹም ቤተክርስቲያኑን በዳግም ለመመለስ አስፈላጊ ያስደረገ ክህደት እንደነበረ እናውቃለን።

ቅዱሳን ማለት የዚህች አባላት እርሱን እንደሚከተሉና የእርሱን ፍላጎት ለማሟላት፣ ትእዛዛቱን ለማክበር፣ እና ከእርሱና ከእኛ አባት ጋር እንደገና ለመኖር ለመዘጋጀት ይጥራሉ ማለት ነው። ቅዱሳን ክርስቶስን በመከተል ህይወታቸውን ቅዱስ ለማድረግ የሚጥሩትን የሚጠቁም ነው።

አዳኝ ለቤተክርስቲያኑ የሰጠው ስም ማን እንደሆንን እና ምን እንደምናምን የሚነግረን ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውዘር አዳኝ እና ቤዛ እንደሆነ እናምናለን። ለኃጢያታቸውን ስሀ ለሚገቡት ሁሉ የኃጢያት ክፍያ ከፈለ፣ እናም የሞትን ሰንሰለት ሰበረ፣ እናም ከሞት መነሳትን ሰጠ። ክርስቶስን እንከተላለን። እናም ንጉስ ቢንያም ለህዝቡ እንዳለውም፣ ለሁላችንም ጊዜ ይህን አረጋግጣለው፣ "በልባችሁ የተፃፈውን ስም ሁልጊዜ እንድትጠብቁ እፈልጋለሁ እላችኋለሁ።" (ሞስያ 5፥ 12)

"በሁሉም ጊዜዎች፣ በሁሉም ነገሮች፣ እናም በሁሉም ቦታዎች" (ሞስያ 18፥ 9) እንደ እርሱ ምስክር እንድንቆም ተጠይቀናል። ይህም ማለት ማንን እንደምንከተልና ለማን ቤተክርስቲያን፣ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ አባል እንደሆንን ለሌሎች ለማሳወቅ ፈቃደኞች መሆን አለብን። አዳኝን በግልፅና በትሁትነት የቤተክርስቲያኑ አባል መሆናችንን በማወጅ ልንከተለው እንፈልጋለን። የኋለኛው ቀ ቅዱሳን --- የኋለኛው ቀን ደቀመዛመርቶች በመሆን እንከተለዋለን።

ሰዎች እና ድርጅቶች በሌሎች ቅልጽ ስም ይሰጣቸዋል። ቅልጽ ስም የስም ማሳጠሪያ፣ ወይም በሰውነት ወይም ሌላ ጸባይ ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ምንም እንኳል ቅልጽ ስም አንድ አይነት የሆነ ክብር ወይም ስልጣን ባይኖረውም፣ ይህን በትክክል ለመቀም ይቻላል።

የጌታ ቤተክርስቲያን በጥንትም ይሁን አሁን ቅልጽ ስም ነበራት። የአዲስ ኪዳን ቅዱስን በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ስለነበራቸው ክርስቲያን ተብለው ይጠሩ ነበር። ስሙ በመጀመሪያ እንደ ስድብ የተጠቀመበት አሁን በልዩነት ይጠቀመበታል፤ እናም የክርስቲያን ቤተክርስቲያን ስም በመጠራት ክብር ይሰማናል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ሊላኛው ምስክር በሆነው በመፅሐፈ ሞርሞን አባሎቻችን ስለሚያምኑ ሞርሞኖች ተብለው ተጠርተዋል። ሌሎችም ቤተክርስቲያኗን ትተው ሌላ ቡድን የሰሩትንም ለመጠቆም የሞርሞን ስምን ይጠቀመበታል። እንደዚህ አይነት ጥቅሞች መምታታት ያመጣሉ። ዜና የሚያስተላልፉት ሞርሞን የሚለውን ቃል ሰዎች ቤተክርስቲያኗን ብዙ ሚስቶች ከሚያገቡት ወይም ከሌሎች ቡድኖች ጋር እንዳያምታቱ ለሚያደርጉት ጥረት እናመሰግናለን። ማንኛውም ከአንድ በላይ ሚስት የሚያገቡ ቡድኖች ወይም መሰረታዊ ሞርሞን ብለው እራሳቸውን የሚጠሩት ከኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው በትኩረት ለመግለፅ እፈልጋለሁ።

ሞርሞን የቤተክርስቲያኑ ሙሉ እና ትክክለኛ ስም ባይሆንም፣ በሚጠሉን መጀመሪያ የተሰጠን ስም ቢሆንም፣ ድርጅቷን ሳይሆን አባላቷን ለመግለፅ ጠቃሚ ሆኗል። ሞርሞን የሚባለውን ስም ለመጠቀም ማቆም አያስፈልገንም፣ ነገር ግን ለቤተክርስቲያኗ ሙሉና ትክክለኛ ስም ትኩረት መስጠት ይገባናል። በሌላም አባባል፣ "የሞርሞን ቤተክርስቲያን" የሚለውን ስም ማስወገድ እና አለመጠቀም ይገባናል።

በአለም ውስጥ የተለያዩ ሀላፊነቶችን ሳከናውን፣ በሞርሞን ቤተክርስቲያን አባል እንደሆንኩኝ እጠየቅ ነበር። መልሴም "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነኝ። በጥንት የአሜሪካ ነቢይና መሪ ስመበተሰጠውና የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ምስክር በሆነው በመፅሐፈ ሞርሞን ስለምናምን፣ አንዳንዴ ሞርሞን ተብለን እንጠራለን" የሚል ነው። በዚህ ጊዜ መልሱ ተቀባይ ነው እናም በእነዚህ እብኋለኛው ቀናት ወንጌሉ እንዴት በዳግም እንደተመለሰ ለመግለፅ እንድችል እድልም ከፍቶልኛል።

ወንድሞችና እህቶች፣ ጌታ እንድናደርግ እንዳወጀው የቤተክርስቲያኗን ሙሉ ስም በመጠቀም መልስ በመስጠት ምን አይነት ተፅዕኖ እንደሚኖረን አስቡበት። ሙሉ ስሙን ወዲያው መጠቀም የማትችሁ ከሆነ፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ነኝ" በሉ እና በኋላም ስለ "የኋለኛ ቀን ቅዱሳንነት" ግለጹ። ።

አንዳንዶች፣ Mormon.org የሚባለውን የኢንተርነት ቦታስ ብለው ይጠይቃሉ። እንዳልኩት፣ አባሎችን በሙሉ ሞርሞን ብሎ መጥራት ተፈቃዲ ነው። ከሀይማኖታችን ውጪ ያሉት እኛን የሚፈልጉት በእዚያ ስም ነው። ነገር ግን Mormon.orgን ከከፈታችሁ በኋላ፣ የቤተክርስቲያኗ ትክክለኛ ስም በመጀመሪያው ገጽ ላይ ይገለጻል፣ እናም

ከእዚያም በኋላ ባሉት ገጾች ላይ በተደጋጋሚ ይታያል። እኛል ለማግኘት ሲፈልጉ የቤተክርስቲያኗን ሙሉ ስም ታይፕ ማድረግ እንዲገባቸው መጠበቁ የማይገባ ነው።

አስፈላጊ የሆኑት ነገሮችን ማድረግ ቢቀጠልም፣ አባላት የቤተክርስቲያኗን ሙሉ ስም በሚያስችለው ጊዜ ሁሉ ለመጠቀ ይገባቸዋል። በቤተሰባችንና በቤተክርስቲያን ስራዎቻችን እናም በየቀኑ በምናደርገው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ጌታ እራሱ እንድንታወቅበት መመሪያ የሰጠው ስም እንደሆነ እንዲታወቅ ማድረግ ልምድ አድርጉት።

በቅርብ በነበረው ቃል ጥያቄ ብዙ ሰዎች ሞርሞን የቤተክርስቲያን አባላቶቻችንን የሚያጠቁም እንደሆነ እንደማያውቁ አሳይቷል። ብዙ ሰዎች ሞርሞኖች ክርስቲያን እንደሆኑ በእርግጥ አያውቁም። በአለም አውሎንፋስ፣ ጎርፍ፣ የምድር መንቀጥቀጥ፣ እና ራዕብ መአት በኋላ ስለሰጠናቸው እርዳታችን ስራዎች ሲያነቡም ጥረታችንን ከክርስቲያን ድርጅት ጋር አያያይዙትም።

በየካቲት 23፣ 2001 ዓ/ም ቀዳሚ አመራር በደብዳቤአቸው እንደጠየቁት፥
“የተገለሰውን፣ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ስም መጠቀም የአዳኝን ስም በአለም ሁሉ ለማወጅ ላለን ሀላፊነት በጣም አስፈላጊ እየሆነ ነው። በዚህም መሰረት፣ ስለቤተክርስቲያኗ ስንናገር በሚቻልበት ጊዜ በሙሉ ሙሉ ስሟን እንድንጠቀምባት እንጠይቃለን።”

በ 1948 ዓ/ም በጥቅምት አጠቃላይ ጉባኤ፣ ፕሬዘደንት ጆርጅ አልበርት ስሚዝ እንዲህ አሉ፥ “ወንድሞችና እህቶች፣ ከዚህ ስትሄዱ፣ ከተለያዩ ሀይማኖቶች ጋር አብራችሁ ትሰሩ ይሆናል፣ ነገር ግን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶችን ስም በመለኮታዊ ትእዛዝ የምትይዝ አንድ ቤተክርስቲያን ብቻ እንዳለች አስታውሱ” (in Conference Report፣ ጥቅምት 1948፣ 167)

ወንድሞችና እህቶች፣ በዚህ ጠዋት ከጉባኤው ስንሄድ ይህንን እንድናስታስ። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ አውቃለህ። በአለም በሙሉ ቤተክርስቲያኑን እንድንገነባ ሀላፊነት የሰጠን እርሱ ነው። ይህም ስሙንም የሚይዝ ነው። ስለዚህ የምመሰክረው በስሙ ነው፣ አሜን።